# <u>የመርዝ እሸት*</u>



ወዳጄ ቢበድለኝ
　　ስጮኽበት ቀለለኝ
ጠላቴ ቢያስቀይመኝ
　　ዝም ኣልኩት እያመመኝ

የጥላቻ ዘር ፍሬ
　　ኣንጀቴ ውስጥ ቋጥሬ
ስዞር በሆዴ ይዤው
　　ረኽቦም ጊዜ ኣርግዤው

ጥቁር እንደ ጥላሸት
　　ኣፈራ የመርዝ እሸት
እሸቱም ባጥሬ ላይ
　　ደርሶ፣ ኣምሮበት ሲታይ



ጠላቴ ከውጭ ኣይቶት
　　በልቡ ተመኝቶት
የኔ መሆኑን ኣውቆ
　　በሩን ኣነቃንቆ

ጨለማን ተኰልኲሎ
　　ገባና ኣጥር ዘልሎ
ጥሬውን ሳያቁላላው
　　እንዳለ ኣሽቶ በላው



ኣየሁኝ በማለዳ
　　ተከፍሎ የቂም ዕዳ
ካጥሬ ስር፣ ከቤቴ
　　ተዘርሯል ጠላቴ

ገ/ኢ. ጕርፉ።

*ከዊልያም ብሌክ ***የመርዝ ዛፍ***
በተባለው ግጥም የተመሰረተ።